## የአእምሮ ሕክምና እኛን እንዲሆን-

# “ሳይካትሪ ‘በተዋሕዶ ከበረ’ !”

“ሕዋ ላይ አይደለም የምንኖረው፤ በቦታ ተወስነን ነው ያለነው። መኖር ማለት ሀገሩን መኖር ማለት ነው፤ማወቅ ማለት የምንኖርበትን ቦታ በትክክል መረዳት ማለት ነው”

ኢድሪስ ሳሐ (2000)

በአሁኑ ጊዜ ዓለማችን ለዘመናት መፍትሔ ባላገኘ የአእምሮ ጤና ችግር ተተብትባ ሳለ፣ ባናቱም በ “ኮሮና ቫይረስ” ምክንያት የተከሰተ አዲስ የአእምሮ ጤና ችግር ወረርሸኝ ውስጥ ትገኛለች። እንደዓለም ጤና ድርጅት የቅርብ ጊዜ ሪፖርት መሠረት ÷ የጭንቀትና የድብርት ሕመሞች በ50% ጨምረዋል። አሁንም ከአራት ሰው፤ አንድ ሰው በአእምሮ ጤና ችግር ውስጥ እየኖረ ነው። በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች የሚኖሩ፤ ከ90% በላይ የሚሆነው የአእምሮ ሕመም ያለበት ሰው የአእምሮ ሕክምና አያገኝም።

በሀገራችን ኢትዮጵያ የአእምሮ ጤናን በትክክል አልተረዳነውም፤ ትኩረት ነፍገነዋል፤ ተገልሏል፤ በቂ በጀት እና የሰው ኃይል አልተመደበለትም። ይህን በዓለም
የተንሰራፋውን የአእምሮ ጤና ችግር ከግምት ውስጥአስገብቶ፤ የዓለም አእምሮ ጤና ቀን “የአእምሮ ጤና ለሁሉም፤ ከፍተኛ የመዋዕለ ነዋይ ፍሰት እና ሰፊ ተደራሽነት ” በሚል መሪ ቃል ይከበራል። ሀገራችን ኢትዮጵያ ለአእምሮ ጤና መስፋፋት የምትመድበውን መዋዕለ ንዋይና ሌሎች ግብዓቶች፤ እንዴት እኛን የሚመስል፣ ሀገራዊ የሆነ የአእምሮ ሕክምና ትምህርትን እና የአእምሮ ጤና አገልግሎትን ለማጎልበት እንጠቀምበታለን? የሚለውን ወሳኝ ጥያቄ በዕውቀት መመለስ ይጠበቅብናል። ዕለቱን፣ የዓለም አእምሮ ጤና ቀንን አስመልክቼም ÷ እኛን የሚመስል የአእምሮ ሕክምና አገልግሎት ለሁሉም ዜጋ ተደራሽ የሚሆንበትን
መንገድ በመጥረጉ ሂደት፣ ቅድሚያ ልንመረምረው ስለሚገባን የአእምሮ ሕክምና ትምህርታችን ሁኔታ እንጨዋወታለን።

እንደ ባሕል ሆኖ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቅድመ ምረቃ የአእምሮ ሕክምና ትምህርትን አስመልክቶ፣ የመግቢያ ትምህርት የሚሰጠው በሙያ፣ በትምህርት እና በዕድሜ አንጋፋ እና አዋቂ በሆኑ የአእምሮ ሐኪሞች ነው። የመግቢያ ትምህርት በሚሰጥበት ቀን፣ ሁሉም የትምህርት ክፍሉ አስተማሪዎች እና የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ÷ ዘመን በማይሽረው ኪነ ጥበባዊ ውበቱ አሁንም ድረስ የብዙዎችን ልብ በሚሰርቀውና በሚያስደምመው የማስተማርያ አዳራሽ፤ ውስጥ ክትት ይላሉ።
ይህ ባሕላዊ የሕክምና ማስተማርያ አዳራሽ ጥንታዊ ከሆኑት የአውሮፓ ማስተማርያ አዳራሾች ወይም ከነሱ “ሌክቸር ትያትር” ጋር በጣም ተመሳሳይነት አለው። ውስጡ ሲገባ የተለየ መንፈሳዊ ኃላፊነትን ይደርባል፣ ልቡናዊ ኩራትን በሰው ላይ ያነብራል። በማስተማርያ አዳራሹ ውስጥ የሚገኙት ቁሳቁሶች፣ ግድግዳው፣ ጠረጴዛው ወዘተ… ከንፁህ ውድ ወይራ እንጨት ነው የተሠራ ነው። መምህሩ ተማሪዎችን ከታች ወደ ላይ ነው የሚያያቸው። ልክ እንደ ብሔራዊ ትያትር፤ የተማሪዎች መቀመጫ ከታች ወደ ላይ ከፍ እያለ እንዲሄድ ተደርጎ ነው የተዋቀረው። መምህሩ ከሚቆምበት ሥፍራ ትልቅ ሰሌዳ አለ፤ አጠገቡም የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ጠመኔዎች ይደረደራሉ። አዳራሹ ሁለት የመግቢያ በሮች አሉት፤ አንደኛው፣ ከላይ በኩል
ያለው የተማሪዎች መግቢያ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ መምህሩ ከሚቆምበት አካባቢ የሚገኝና መምህሩ ሥራ ከሚሠራበት አካባቢ በቀላሉ እንደ ትያትር ተዋናይ መድረኩ ላይ ጉብ የሚያደርገው ነው።

የመማርያ አዳራሹ አሠራር በብዙ የሀገራችን ዩኒቨርሲቲዎች የተለመደው እና አሁን አውሮፓውያኑ ገሸሽ እያደረጉት ያለው ባሕላዊውን “ አስተማሪ ተኮር ” ተብሎ የሚጠራውን የትምህርት ዘዴ፣ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጀ ይመስላል። ብዙዎች ባለፍንበት በዚህ የማስተማር ዘዴ በዕውቀት መካኑ ቀርቶብን እንደነገሩ እንኳን ለመተግበር፤ በተለይ
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ዳተኛ የሆንን ሁሉ
ያስመስላል፤ እስከዛሬም ድረስ ዓይናችንን በወጉ መክፈት የቻልን አይመስለኝም። የዛሬው የአእምሮ ሕክምና ትምህርት ግን፤ ምንም እንኳ የአዳራሹ ቅርጽ በተቃራኒው አስተማሪ ተኮር የሆነየማስተማር ዘዴ ተጠቅሞ እንዲያስተምር መምህሩን ቢገፋፋውም፣ የአእምሮ ሕክምና አስተማሪው ትምህርቱን እንደሁልጊዜውም የተለየ ችሎታውን ተጠቅሞ “ ተማሪ ተኮር ” ነበር ያደረገው። በዚህ ትልቅ አዳራሽ የተማሪዎች አቀማመጥ ከታች ወደላይ በሆነበት ትምህርቱን ከ “ አስተማሪ ተኮር ” ወደ “ ተማሪ ተኮር ” የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ መቀየር መቻል ትልቅ በራስ መተማመንን እና ድፍረትን ይጠይቃል-ጠይቋልም። ለነገሩማ፣ “ ከልብ ከፈለጉ መንገዱ ቀና ነው” መባሉስ ለዚህ አይደል?

የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች የአእምሮ ሕክምና ትምህርት ለመማር ለመጀመርያ ጊዜ ሲመጡ ለአእምሮ ሕመም ያላቸው ግንዛቤ እና አመለካከት ብዙ ጊዜ ከማኀበረሰባቸው የወረሱት በመሆኑ፣ ልክ እንደ ማኀበረሰቡ የአእምሮ ሕመምተኞች “ አደገኛ፣ ተደባዳቢ፣ ጥቅም የሌላቸው፣ ፅዳታቸውን የማይጠብቁ፣ ትርጉም ያለው ነገር የማይናገሩና ያልተጠበቁ ነገሮች ሊከውኑ የሚችሉ እንደሆኑ ወዘተ.፣” አድርገው ስለሚገነዘቧቸው፣ ይህን አመለካከት በሳይንሳዊ ዕውቀት አስደግፎ የተሻለ ግንዛቤ እንዲያመጡ የሚደረገው ጥረት፣ ብዙ ማገዶ የሚፈጅ፤ የስድስት ሳምንታት ጎታች ሐሳብን አፍርሶ በአዲስ ሐሳብ ለመተካት የሚደረግ እልህ አስጨራሽ ሒደት ነው። እዚህ ላይ፣ የዚህን ጽሑፍ አዘጋጅ፣ የሕይወት ልምድና የማስተማር ተመክሮ ማንጸሪያ አድርገን፣ ከዕለቱ የአእምሮ ሕክምና ቀን “ የአእምሮ ጤና ለሁሉም፤ ከፍተኛ የመዋዕለ ነዋይ ፍሰት እና ሰፊ ተደራሽነት ” መርሐ ጋራ አጋብተንና አግባብተን፣ ስለ ክፍል ውስጥ መስተጋብሮች
እንደሚከተለው እናወጋለን።

የመግቢያ ትምህርቱ የጀመረው የተማሪዎችን ስም በመጥራት ሲሆን፣ የአእምሮ ሕክምና ክፍሉ አባላት ጋራ ትውውቅ ተደረገ። መምህሩ፣ በሚቀጥሉት ስድስት ሳምንታት ከተማሪዎች ምን እንደሚጠብቅ ሰፊ ማብራርያ ከሰጠ በኋላ፣ የትምህርቱን ፍሰት ወደ ተማሪ ተኮር ዘዴ በመቀየር፣ “ እስኪ በምትኖሩበት ማኅበረሰብ ውስጥ ለአእምሮ ሕመምተኞች ተሰጥተው የሚነገሩ ስሞችን አብረን እንዘርዝር?” ብሎ ጠመኔውን አንስቶ ወደ ሠሌዳው ተጠጋ። የሠሌዳውን አለመፅዳት ተመልክቶም አንዱን ተማሪ ሠሌዳውን እንዲያፀዳለት እያደረገ ተማሪዎቹን፣ “ከጠመኔ እና ከጥቁር ሠሌዳ ወይስ ከኮምፕዩተር እና ከፕሮጀክተር በየቱ ማስተማር ይሻላል?” ብሎ ጠየቃቸው። ብዙዎቹ ወጣት ተማሪዎች የቴክኖሎጂ አፍቃሪ ስለሆኑ፣ ኮምፒዩተር እና ፕሮጀክተርን መርጠው ምክንያታቸውን ሲያስረዱ “ በፕሮጀክተር ሲሆን ‘ጽሑፉ ያምራል’፣ ‘አድካሚ አይደለም’፣ ‘የጠመኔው ብናኝ እጅ እና ፊት አያቆሽሽም’” እያሉ አሳማኝ ያሉትን ሐሳብ ደረደሩ። አንድ ከሁሉም ተማሪዎች በዕድሜ በለጥ የሚልና ከገጠሪቱ ኢትዮጵያ የመጣ ተማሪ ከአብዛኛው ተማሪ በተለየ ጠመኔ እና ጥቁር ሠሌዳ እንደሚሻል መርጦ ምክንያቱንም የተለመደ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ እንደሆነ፣ መብራት ቢጠፋ፣ ኮምፒዩተር እና ፕሮጀክተር ባይሠራ፤ የአስተማሪ ጭንቅላት፣ ጠመኔ እና ጥቁር ሠሌዳ እስካሉ ድረስ ሁሌም ትምህርት ይኖራል በማለት አስረዳ። አስተማሪው ሁሉንም አዳመጠና፤ “አንዳንዴ ብዙኃኑ ተሳስቶ ጥቂቶች ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ፤ እኔም የመጨረሻውን ሐሳብ እደግፋለሁ፤ ለእኔ ጠመኔ እና ጥቁር ሠሌዳ Low Tech, High Impact ያለው ቴክኖሎጂ ነው! ” ብሎ ሐሳቡን ገለፀ። ሠሌዳውን ያፀዳለትን ልጅ አመስግኖ መጀመርያ የጠየቀውን ጥያቄ በድጋሚ ጠይቆ ጠመኔውን ይዞ ወደ ጥቁር ሠሌዳው ተጠጋ። ወጣት ተማሪዎቹ እንደ ሁልጊዜው በመደንገጥ ይሁን በመተፋፈር በአዳራሹ ከፍተኛ ዝምታ ሰፈነ። አንዳንዱ ተማሪ አንገቱን ደፍቶ እየጻፈ እንደሆነ ያስመስላል፤ የተቀረው ወደ ሰሌዳው አፍጥጧል። የአገራችን የትምህርት ሥርዓት ከጀማሪ ክፍል አንስቶ አስተማሪ ተኮር ስለሆነ እና ተማሪዎች በዚያ ስላደጉ በትምህርት ክፍለጊዜ የተማሪዎቹን ተሳትፎ ማግኘት ሁሌም ከባድ ነው። ብዙ ጊዜ አገሩን የማያውቅ ተጋባዥ የውጭ ሀገር መምህር እንደ አገሩ መስሎት ጥያቄውን ያዥጎደጉደው እና እነ “ዝም አይነቅዝም” ዝም ሲሉ፣ ክፍሉ በፀጥታ ሲዋጥ፣ ፈረንጁ አስተማሪ ግራ ይጋባል። የፊቱ ቆዳ ቀለም ይቀያየራል፤ ምንተእፍረቱን ፀጥታው አስፈርቶት እና ትምህርቱን እንዴት ማስቀጠል እንዳለበት ግራ ገብቶት፣ ጥያቄውን ወደ እኛ፤ እሱን ልንረዳ ወደመጣነው አስተማሪዎች ያዞረው ነበር። መምህሩ የተማሪዎችን ዝምታ ለመስበር ጥያቄውን ደገመላቸው እና “ እስኪ መልሱን ለራሳችሁ አሰላስሉ ወይም አጠገባችሁ ካለ ተማሪ ጋር ተወያዩበት፤ ሦስት ደቂቃ ሰጥቻችኋለው” አላቸው። በማስተማር ዘዴ ላይ የተሠሩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በትምህርት ዓለም ሁለት ዓይነት ተማሪዎች አሉ።

የመጀመርያዎቹ “ጮክ” ብለው የሚያስቡ፣ አጠገባቸው ካለ ተማሪ ጋራ በጥያቄ ዙሪያ መወያየት የሚፈልጉ ሲሆኑ፣ ሁለተኞቹ ደግሞ “ለራሳቸው” በውስጣቸው ማሰላሰል የሚፈልጉ ናቸው። ሁለቱም ዓይነት ተማሪዎች ጥያቄ በመምህሩ ከተሰነዘረ በኋላ ከአንድ እስከ ሁለት ደቂቃ ያህል የማሰላሰልያ፣ የመወያያ እና የማሰብያ ጊዜ ይፈልጋሉ። ስለዚህ፣ ከጥያቄ በኋላ ተማሪዎች በትጋት እንዲሳተፉ የማሰላሰያ ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል። መምህሩም ይህን ነበር ያደረገው። ከሦስት ደቂቃ ማሰላሰል በኋላ ተማሪዎቹ በትጋት እና በንቃት በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉትን የአእምሮ ሕመምተኞች ስም ለመጥራት በተለያየ አቅጣጫ እጃቸውን አወጡ። አስተማሪው አንድ ቀደም ቀደም ለሚል፤ ከኋላ ለተቀመጠ ልጅ ዕድሉን ሰጠው። ተማሪው በግራ እጁ ያደገ እና የተቆጣጠረ ፀጉሩን እያፍተለተለ እንዲህ አለ፤ “በእኛ አካባቢ እነኚህን ‘ሰዎች’ ፍሬን የበጠሰ፣ ሾጤ፣ አንዳንዴም ጡዘታም እንላቸዋለን” ብሎ ፈገግ አለ። አስተማሪው በውብ የአማርኛ ጽሑፉ ሠሌዳው ላይ ከጻፈ በኋላ፣ ወጣቱን ተማሪ “አሁን ከዘረዘርከው ስም ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚነገር ቋንቋ የሚመዘዘው የቱ ነው? ” ብሎ ጠየቀው። ተማሪው ግራ እንደመጋባት ብሎ፣ “እኔ እንዳየሁት ከኳስ ሜዳ እስከ መሳለሚያ፣ ከሽማግሌ አስፋልት ላይ እስካለ ‘ፈላ’ ድረስ እነኚህን ‘ሰዎች’ በዚህ ስም ነው የሚጠሯቸው” ብሎ ፀጉሩን በቀኝ እጁ ማፍተልተል ቀጠለ። አስተማሪው “ፈላ” ያለው ቃል ግራ ገብቶት “ አንተ ልጅ በአማርኛ አውራ እንጂ!... የአንተን ቃላት የደስታ ተክለወልድ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት አያውቃቸውም … ” ብሎ፤ በእሱ ትውልድ እና በአዲሱ
ትውልድ መካከል አማርኛ ቋንቋ እንዴት እንደተለወጠ እያሰበና በጣም እየተገረመ ለሚቀጥለው ተማሪ፣ እጁን ላወጣዉ ልጅ ዕድሉን ሰጠው።

ይሄኛውም ተማሪ የራሱን ፀጉር ወደ ግንባሩ አምጥቶ እያፍተለተለ “ በእኔ አካባቢ ዕብድ፣ ጨርቁን የጣለ፣ ንክ፣ ወፈፌ እንላቸዋለን” አለ እና ሲቃ እየተናነቀው፤ “በዚህ ስም መጠራታቸው ትክክል ነው ብዬ አላምንም፣ የታማሚዎቹ የቅርብ ዘመድ ብቻ ስንሆን ይመስለኛል ትክክል አለመሆኑ የሚገባን ” ብሎ ዝም አለ። አስተማሪው ለድፍረቱ፣ ለተለየ አተያዩ ተማሪውን አመስግኖ፤ ለምትቀጥለው በዕድሜ ከሁሉም ተማሪ ትንሽ ለምትመስለው ተማሪ ዕድሉን ሰጣት። እሷም ቀና ብላ በእንግሊዝኛ ቅላፄ እና ላላ ባለ አማርኛ “ በእኛ ቤተሰብ ውስጥ እንደዚህ ዓይነት ሰዎችን ‘ክሬዚ’ ነው የምንላቸው ” አለች። አስተማሪው ያለችውን መጠርያ ጥቁር ሠሌዳው ላይ ከጻፈ በኋላ የት አካባቢ እንደምትኖር ጠየቃት። ቦሌ አካባቢ ስትል በመገረም አንገቱን ነቅንቆ፤ ለሌላ ከምስራቅ ኢትዮጵያ ለመጣ ተማሪ ዕድሉን ሰጠው። ተማሪው አንገቱን ቀና አድርጎ “በእኛ ከተማ እነኚህን‘ዘመዶቻችንን’ መጅኑን፣ ጀዝባ አንዳንዴም እንደሁኔታው መራቱ እንላቸዋለን፤ ነገር ግን ወጣም ወረደም እኛም አንዳንዴ እንደነሱ ስለምንሆን ‘ ዘመዶቻችን ’ ናቸው ” ብሎ የሚስቁት ከጎኑ የተቀመጡ ተማሪዎች ላይ አፈጠጠባቸው። አስተማሪው “ ዘመዶቻችን ” የሚለው ገለፃ ልቡን ስለነካው ወደ ተማሪው ዞር ብሎ “ልክ ነህ! የሁላችንም ቤት መቼ

እንደሚንኳኳ ስለማናውቅ፣ ሁሉም ዘመዶቻችን ናቸው” አለው፡፡

በመቀጠል ሐሳቡን እንዲገልፅ ዕድል የተሰጠው ከመጀመርያ ዓመት የሕክምና ትምሕርቱ ጀምሮ የእኔ ወዳጅ የሆነው በእሱ አገላለፅ “ከቅኔ ትምህርት ዊዝድሮው አድርጎ” የሕክምና ትምህርትን የተቀላቀለው ስንሻው ነው፡፡ ተደጋጋሚ የቅኔ ዘረፋ ባቀጠነው ድምፁ “እነኚህ ‘የእኔ ቢጤዎች’” ብሎ ሲጀምር ተማሪው በሙሉ ሳቁን ለቀቀው፡፡ አስተማሪው ተቆጣ፤ “ ለምንድነው ሐሳብ የምታቋርጡት? እናንተን ከማስተማር የመዋዕለ ሕፃናት ተማሪ ማስተማር በስንት ጣዕሙ! … ስሜታችሁን መግራት የምትጀምሩት መቼ ነው? ይቅርታ ስንሻው ቀጥል” አለው፡፡ “አዎ! … በድጋሚ እነኚህ ‘የእኔ ቢጤዎች’፣ ‘የእናንተ ቢጤዎች’ አላልኩም፤ በእኛ አካባቢ አብሿም፣ መተት የተመተተበት፣ ቡዳ የበላቸው ብለን እንጠራቸዋለን” ካለ በኋላ፣ ጉሮሮውን ጠረግረግ አድርጎ በለሰለሰ ድምፅ እንዲህ አለ “ እነኚህ የአእምሮ መናወፅ ያለባቸው ሰዎች በፈጣሪ አምሳል የተፈጠሩ እንደኛው ሰዎች ናቸው፤ ለእዚህ ነው ‘የእኔ ቢጤ’ ያልኳቸው፡፡ አንዳንዴም ከእኔ ይሻሉ ይሆን? ብዬ አስባለሁ፤ ምክንያቱም ማስመሰል እና ዋሾነት አላይባቸውም” አለና አንገቱን አቀረቀረ፡፡ የተቀሩት ተማሪዎች ተራ በተራ ዕድል ሲሰጣቸው፤ የአእምሮ ሕመምተኞች መጠርያ ናቸው ብለው ለክፍሉ ከአጋሩት መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡- የፈዘዘ፣ ወፈፌ፣ ዕቃ የሰበረ፣ ቀዌ፣ ጠሸ፣ ጂንያም፣ የነበዘ፣ የዞረበት፣አማኑኤል፣ ቢጩ፣ ባለዛር፣ ወዘተ.ተማሪዎቹ መጠርያ ናቸው ብለው ያቀረቧቸው ቃላት ወይም ስያሜዎች በአብዛኛው አማርኛ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ግን ሀገር ውስጥ ከሚነገሩ ቋንቋዎች የተወረሱ ይመስላሉ፤ ከሁሉ የሚገርመው አንዳንዱ ቃላት በየትኛውም ቋንቋ የማይነገሩ አዲስ የተፈጠሩ ቃላት ይመስላሉ፡፡ በመቀጠልም፣ መምህሩ ከላይ የተዘረዘሩ በማኅበረሰቡ የሚነገሩ ስሞች ተማሪዎች በሚያንፀባርቁት ባሕርይ፣ ስሜት፣ እና ሐሳብ በተጨማሪም ለማኅበረሰቡ ያላቸውን ትርጉም መሠረት አድርገው ተማሪዎቹ እንዲገልጿቸው አደረገ፡፡ ተማሪዎች በገለፃቸው እያንዳንዱ በማኅበረሰቡ የሚሰጡ ስሞች በሕመሙ ዓይነት፣ ትልቅነት እና ስፋትም ለማኅበረሰቡ የተለያየ ትርጉም እንዳላቸው ካሳዩ በኋላ ማኅበረሰቡ ያንን መሠረት አድርጎ ሕሙማኑን ሲፈልግ እንደሚያገል፣ ሲፈልግ እንደሚያሳክም፣ ሲያሻው ፀበል እንደሚወስድና እንደሚመግብ፣ ካላሻው አስሮ ቤቱ እንደሚያስቀምጥ፣ ወዘተ. አስረዱ፡፡ እንደማጠቃለያ፣ መምህሩ የተዘረዘሩትን ስሞች አውሮፓ ተኮር ከሆነው የአእምሮ ሕመም ምደባ ጋር አነፃፅሮ እግረ መንገዱን አገራዊ የሆነውን የአእምሮ ሕመም የስም አጠራር እና ምደባ ከምዕራባውያኑ ጋር እያያያዘ ገለፃ አደረገላቸው…“ሳይካትሪ በተዋህዶ ስለመከበሩና ሌሎች የአእምሮ ሕክምና ትምህርት የማስተማር ተመክሮዎችን ” ሰንቄ፣ በሚቀጥለው ጽሑፍ እስክንገናኝ፣ “ የአእምሮ ጤና ለሁሉም፤ ከፍተኛ የመዋዕለ ነዋይ ፍሰት እና ሰፊ ተደራሽነት” በሚለው በዘንድሮ የዓለም አእምሮ ጤና ቀን መሪ ቃል ድምፄን ከፍ አድርጌ በማስተጋባትና መልካሙን ሁሉ በመመኘት እሰናበታለሁ፡፡